# እነ ነውር ጌጡ በባንዳ ፍቅር አበዱ!

የኔ ብአዴን ቆንጆዬ ነው! ያንተ ካካ ነው!

ሳይዘሩ እንደ አረም ተሰብል የበቀሉ፣
ማጭድ ዛቢያ ወደው ይነታረካሉ፡፡

ማጭድን ወሽሞ ሰብልን ያሳጨደው፣
የማጭዱ ዛቢያ መሆኑን እረስተው፣
አረሞች ከነፉ ከሀዲ እንጨት ወደው፡፡

ይኸንን አላዩ ይኸንን አልሰሙ፣
እነ መዩ ካሳ አባ ዳኘው ጥቁሩ፣
ንጉስ ሚካኤልም ራስ አዳል ተክሉ፣
አባ ኮስትር በላይ የአገር ደም መላሹ፣
አንዳንድ ልጆቻቸው ባንዳ ሲወሽሙ፣
በውሽማቸውም እርስ በርስ ሲባሉ፡፡

እነ ነውር ጌጡ ሐፍረት የሌላቸው፣
ለሎሌው ብአዴን የጭን ገረድ ሆነው፣
የጀግኖችን ልጆች እየጠለፉ ነው፣
ተፋኖ ወይራ ሥር እንደ ጠሮ በቅለው፡፡

ተምን ቁጢትና ተመን ክር ቢሰሩ፣
የአህያ ያህልም ትንሽም ሳያፍሩ፣
“የኔ ባንዳ ቆንጆ ያንተ ባንዳ ካካ” እየተባባሉ፣
ጎጥ ላይ ተቸክለው ይነታረካሉ?

ባእዴን ያፈቀርሽ አንቺ ወሮ በላ፣

ባእዴን ያፈቀርክ አንተ ወለወልዳ፣
የአማራ አጽም ቆርጥመህ ደሙን ልትጠጣ፣
ሲረግምህ ይኖራል ሲልህም ይሁዳ፣
ታሪክ በመዛግብት ትውልድም በዜማ።

እስተዘላለሙ መቃብር የምትኖረው፣
በክህደት ተግባርህ ብዕር ሲጭርህ ነው፣
ይኸንን ታላመንክ ይሁዳን ጠይቀው።

ሰላሳ ዲናርህን ላፍ አድርገህ ወስደህ፣
ያሳደገህን ሕዝብ ሙልጭ አርገህ የካድህ፣
ለሎሌው  ብአዴን ሎሚ የወረወርክ፣
በምድር ላይ ታሪክ በሰማይ ቤት አላህ፣
እስከ ዘላለሙ ችሎት ነው እሚያቆሙህ።

ጊዜዋ እስከትመጣ መቃብር እስክትገቡ፣
የብአዴን ውሽሞች እርስ በርስ ተባሉ፣
ባንዳን አፍቅራችሁ ጨርቅ ጥላችሁ ሂዱ፣
እነ ነውር ጌጡ መቼም ሰው አትሆኑ፣

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
መስከረም ሁለት ሺ አስራ አምስት ዓ.ም.